# <u>በአጋጣሚ ያበጠች ፊኛ ፤ በትንሽ እሾህ ተነፍሳ፤ ብትክትኳ ይወጣል !</u>

ሐተታ ቁ 2

ግንቦት 2006 ዓም

በወቅቱ የተከሰቱት የዓለም አቀፍ ፤ የአካባቢና የሀገር ውስጥ ሁኔታዎች ተደማምረውና ተገጣጥመው በመምጣታቸው ፤ የደርግን ወታደራዊ አምባገነን ሥርዓት ባልተጠበቀ ፍጥነትና ባልታሰበ ሁኔታ በማንኮታኮት ፤ የኢትዮጵያን የፖለቲካ መልከዐ- ምድር ለወጡት ። የወታደሩ አምባገነን አገዛዝ ተወግዶ በዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ከተተካ፤ ይኸው ዛሬ ሃያ ሦስት ዓመታት ተቆጥረዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ሲል ፤ የአካልና የኀይወት መሥዋዕት እየከፈለ ለአስራ ሰባት ዓመታት ታገለ። ሀብት ንብረቱ ወደመ። ለጆቹም እንደ ጭዳ ታረዱ። ባኅሉ፤ ታሪኩ፤ ዕምነቱና እሴቱ፤ ሃላፊንትንና ተጠያቂትን ባላነገቡና አርቆ ማስተዋልንም ባላተረዱ እፍኝ በማይሞሉና የዝቅተኝነት ስሜት በተጠናዎታቸው ምንደኞች ተበወዘ፤ ተዋረደ፤ ለውጭ ሰዎች መጫዎቻ እንዲሆን ተዳረገ ። ሀገራችንም ለባዕዳን ፍላጎት ቤተ-ሙከራ እንድትሆን ተደረገ።

ይህንን የደርግ የጥፋት ደርጊት የተቃወሙትን፤ ከሀገሪቱ ከፈተኛ ወታደራዊ የትምህርት ተቋማት፤ ማለትም፤ ከሐረር ጦር አካዳሚ፤ ከአየር ሃይል ትምህርት ቤት ፤ ከባህር ኃይልና ከኢትዮጵያ ፓሊስ አካዳሚ ገብተው ከፍተኛ ትምህርት የቀስሙትን ምሁራን መኮንኖች ሽጨፈጭፏቸው ። ያን የመሰለ የሀገሪቱ መከላከያ ሠራዊትም የማህይማን ካድሬዎች መጫዎቻ አደረጉት ። የዚህም ውጤት ምን እንደሆነ ታሪክ የመዘገበወና ሕዝቡም የሚያውቀው ስለሆነ፤ ያንን መደጋገሙ ለጊዜው ፋይዳ የለውም። መናልባትም ለተተኪው ትውልድ ትምህርታዊ ጠቀሜታ የሚሰጥ ከሆነ ግን መዝግቦ ማለፉ አስፈላጊ ይሆናል።

በጊዜው ሥልጣን ላይ ተንሰራፍፈው የነበሩት አጥፊ ቡድኖች ፤ የሀገሪቱን ሉዋላዊናትና ኅልውና የሕዝቡንም አንድነትና ደኅንነት ለከፍተኛ አደጋ አጋልጠው ሸሹ። ከሰሙ። ደርግን ከፉ እየመከሩ ገደል ውስጥ የጨመሩት እኩይ ባዕዳንም ሆኑ የሀገር ውስጥ ባንዳ ጠላቶች ፤ የልባቸውን ካደረጉ በኋላ፤ ደርግን አጋልጠው ወደ ሚሄዱበት ሄዱ። በእነርሱና በደርግ ትብብር መንስዔ የመጨርሻው ተጠቂዎች የሆኑት ግን ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ ሆነው ቀሩ። ደርግም ሆነ፤ ባዕዳን አለቆቹና ሀገር-በቀል ባንዳዎች የተከሉት አሜካልም ግን፤ መርዙ ይኸው እስካሁን ድረስ አልጠፋም። በዚህም ምክንያት፤ የዛሬው ትውልድ ሰብሳቢና አቋጣሪ በማጣት በማንነት ፍለጋ ከርታታ ዜጋ እንዲሆን ተደርጓል። ለተንከራታችነቱ ምክንያት ደግሞ፤ ብዙ ፈርጆች አሉት። እነርሱም፤ ታሪክ አልባ ዜጋ እንዲሆን መደርጉ፤ በደርግ አርምኒያዊ ጭሽጨፋ ምክንያት ፈርቶና ተሸማቅቆ እንዲያድግ መደረጉ፤ ደርግን የተካውን፤የወያኔ ዘርኛ አገዛዝ በቆርጥነት ለመታገል አለመቻሉ፤ በኢትዮጵያዊ ማንነቱ እንዲጠራጠር መደረጉ፤ ለግል ኑሮውም ሆነ ለብሄራዊ ዓላማው እንዳያስብ፤ አቅጣጫ አልባ እንዲሆን መደርጉ ከዋና ዋና ብሄራዊ በደሎች መካከል በግምባር-ቀደም ተጥቃሾች ሆነዋል።

በማነኛው ሥርዓት መንግሥትም ሆነ በመቸውም ወቅት ፤ አንድ ሀገርና ሕዝብ፤ ነጻነቱንና ኅልውናውን በሚመለከት፤ በባዕዳን ሃይል መተማመን እንደማይኖርበት የደርግ አገዛዝ ፤ በዓሉታዊ ገጽታው እንኳን ቢሆን፤ ቋሚ ትምህርት ትቶ ሄዷል። ወትሮዉንም ቢሆን እኮ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ፤ ነጻነቱን አስከብሮ፤ ታሪኩንና ባኅሉን፤ እምነቱንና ዕሴቱን ጠብቆ፤ የሀገሩን ሉዋላዊንትና የግዛት አንድነትን ተከላክሎ በመጠበቅ ለአያሌ ዘመናት የኖረው፤ በራሱ መሥዋዕትነት <u>ብቻ</u> በመተማመኑ ነበር ። አለመታደል ሆኖ ፤ የቅርብ ጊዜ የሀገሪቱ ገዥዎች ፤ ሕዝብን እየገዱና ሀገርንም እያጠፉ በሥልጣናቸው ለመቆየት ሲሉ ፤ በግድ የባዕዳንን ርዳታ ማግኘትን አስፈለጋቸው ። ይህ ድርጊታቸው ደግሞ ሀገራችንን በተዘዋውሪ መንገድ፤ወደ ቅኝ ግዛት ደረጃ እንድትወድቅ አድርጓት ቆይቷል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ፤ በሀገራችን የተፈራረቁት ገዥዎች ይህንን ሲያደርጉ ለመቆየታቸው መስረጃ የሚያስፈልገው ድርጊት አይደለም። ይህ ተንበርካኪነት ግን ከወያኔ ውድቀት በኋላ የሚቀጥል አይሆንም። ምን ጊዜም ቢሆን፤ ሀገራችን፤ ዴሞክራሲያዊና ሀገር ወዳድ መሪዎችን ካላበቀለች፤ ከባዕዳን ነጻ ትሆናለች ማለት ዘበት ነው።

ይህ ዕውነታ እንደታጠበቀ ሆኖ ፤ የውጭ ሁኔታዎች በአንድ አገር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ ተጽዕኖ አያሳድሩም ማለት ግን አይደለም። ተፈልጎም ይሁን ሳይፈለግ ፤ ቀላልም ይሁን ከባድ ተጽዕኖ ያመጣሉ ።የቀድሞው ሶቬየት ኅብረት መፈረካከስ በሀገራችን ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ ሀገር ያወቀዉ በመሆኑ፤ ያንኑ መዘርዘር አስፈላጊ አልሆነም።

የሶቬየት ኅበረት መንኮታኮት፤ የደርግ መፈረካከስና የምዕራባውያኑም መተባበር ጠቅሚቸው፤ በዘር ተደራጅተው የመጡት ወያኔዎች ፤ ወደ ምንሊክ ግቢ ሰተት ብለው ለመግባት በቅተዋል። ለአለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት፤ ዎያኔዎቹ በኢትዮጵያ ሕዝብና በሀገሪቱ ላይ የፈፀሙትን ግፍ፤በደልና ወንጀል በዚህ ሐተታ ማዘርዘር፤ ዐባይን በጭልፋ ስለሚሆን ለጊዜው አቆይተነዋል።

“ በኢጋጣሚ የተነፋች ፊኛ፤ በትንሽ እሾህ መተንፍሷ” ን ባለማወቃቸው እነኝህ አጥፊዎች ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብና በሀገሪቱ ላይ፤ ለታሪክና ለትውልድ የሚተላለፍ ወንጀል በመፈጸም ላይ ይገኛሉ ። ወቅቱንም እያጠበቀ የሚፈንዳ የዘረኝነት ቦምብ በመቅበር ላይ ናቸው። በአብዛኛው ቦታም አደገኛውን ቦምብ ቀብረው ጨርሰዋል። በሕዝብ በጎ ፈቃድና ተብብር ላይ ሳይሆን፤ በባዕዳን ኃይል በተደገፈ ነፍጥ በመተማመን ብቻ የተያዘ ሥልጣን ፤ የኋላ-ኋላ፤ በሕዝብ አመጽ፤ ጃርት እንደበላው ዱባ መፈረካከሱ አይቅሬ ነው። ባጋጣሚ የተነፋች እፊኛ በትንሽ እሾህ ተበስታ ብትክትኳ መውጣቷን ያለመረዳት መንሰዔው፤ ከድንቁርና የመነጨ ትዕቢትና ከንቱነት መሆኑን የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ በሚገባ አረጋግጧል ። በየካቲት 66 ዓም አብዮት ወቅት፤ የሕዝቡን አለመደራጀት አጋጣሚ በመጠቀም፤ደርግ በግርግር የሕዝብን ትግል ነጥቆ፤ ለራሱ ሥልጣን መቆናጠጫ ተጥቅሞ፤ በኢትዮጵያ ላይ ያወረደውን መዓት የታሪክ መዛግብት ዘግበውታል። ያም ሆኖ፤ በመጨረሻ ፤ ደርግ ያግበሰበሰው ሥልጣን ከሕዝብ ቁጣ አላዳነውም። ወያኔዎቹም የደርግ ዕጣ-ፈንታ እንደሚጠብቃቸው ሊረዱ አልቻሉም። የሥልጣን ፍቅር፤ ዐይነ -ኅለናን ስለሚያደናብር፤ ወያኔዎቹ እስከ በመጨረሻ ግበኣተ- መሬታቸው ደረስ እየተቅለበለቡ መጠራሞታቸው አይቀርም። የኋላ ኋላ ዕውነት ይረታ እንደሚባለው፤ በመጨረሻ አሸናፊ የሚሆኑት ግን ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ ብቻ ናቸው !

የኢትዮጵያ አጥፊዎች ግን በአስራ-አንደኛው ሰዓት ከኢትዮጵያ ሕዝብ የአመጽ ቁጣ ሊያድናቸው የሚችል ምድራዊ ኃይል አይኖርም። ይህንን ታሪካዊ ሀቅ ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ፤ " ውርድ ለራሴ" ብሎ ተጠባብቆ ይጠብቅ ! አንድነቱን ሳያናጋ ይሰንብት! ሀገሩንም ሳትከፋፈል ተባብሮ ካጥፊዎቿ የከላክል! በረዥም አኩሪ ታሪኩ፤ ታሪክ እየሰራ እንደኖረ ሁሉ፤ ዛሬም የሚቅጥለውን ታሪክ እየሰራ የሀገሩን ጠላቶች ያሳፍር ! እንደ ቀደምት ወላጆቹ ሁሉ፤ እርሱም ለተተኪው ትውልድ አኩሪ ታሪክን አስረክቦ ይለፍ ! አኩሪ ታሪክ አውርሶ የሚያልፍ ትውልድ፤ አኩሪው " ስሙ ከመቃብር በላይ " እንደሚኖር አይዘንጋ !

ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ ካስከባን ዘንዳ፤ ታዲያ ምን መደረግ አለበት ? መፍተሄውስ ምን ሊሆን ይችላል ? ብልሃቱስ ከየት ነው የሚመጣው ? እነኝህንና የመሳሰሉትን ሁሉ የመውያየትና መልሱንም የማግኘት ኃላፊነት የማን ሊሆን የገባል ? ጥያቄዎቹ በአግባቡ ተመለሱም አልተመለሱ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በኩል ግን አንድ የመጨረሻ ደምዳሜ ተደርሷል ። የሀገሪቱ ልሂቃን፤ የሕዝቡን ቁስልና የልብ ትርታ በሚግባ ተረድተው፤ በመፍተሄው ፍልጋ ላይ ካልተባበሩ፤ ብሎም ኢትዮጵያን ከተቃጣባት አደጋ ካላዳኑ፤ " ጀብ ከሄደ በኋላ " የሚጮኸው የውሻ ጩኸት እርባና አይኖረውም ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ሁሉንም አይቶና ታዝቦ አሁን በአንድ አማራጭ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተገድዷል ። ይኸውም፤ ወያኔ በመጨረሻው የመጥፊያ ዘመኑ፤ እስከዛሬ ሲቀብረው በኖረው የጥላቻ ቦምብ አማካኝነት፤ ሕዝቡን እርስ በርስ እንዳያፋጅና ሀገሪቱንም ወደ መጨረሻው አዘቅት እንዳይከታት፤ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ፤ ሀገሩን ከተቃጣባት አደጋ የመከላከል ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ነው። ይህ ድምዳሜ ተስፋ የሚሰጥ ቢሆንም ቅሉ፤ ዕፎይታን የሚሰጥ ሊሆን ግን አይችልም ። ለአያሌ ዘመናት በሠላም ተባበሮ፤ ትጋብቶና ተዛምዶ በአንድነት የኖረውን ሕዝብ፤ የውጭ መሰሪዎችና ሀገር-በቀል አጥፊዎች ሊአጠፉት እንዳማይችሉ በታሪክ ተደጋግሞ የተመሰከር ክስተት በመሆኑ፤ ሁሉም ዜጋ ሊጽናና ቢችልም እንኳ፤ በሌሎች ሀገሮች ላይ የተካሰተው ዓይነት ጥፋት ሀገራችንን አያሰጋትም ብሎ መዘናጋት እንደማያስፈልግ፤ ስጋታቸውን የሚገልጹ የሀገርና የውጭ ሀገር የፖለቲካ ተንታኞች በርካታ ናቸው።

ታዲያ፤ እዚህ ድምዳሜ ከተደረሰና በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የሚያንዣብበውን የጥፋት ጭጋግ ለመግፈፍ አስፈላጊው ሁሉ መደረግ ያለበት መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም ። በመሆኑም የሚከተሉትን ርምጃዎች መውሰድ ለነግ-ተነገወዲያ የሚተው አልሆነም። ስለዚህ ፤ ከታች የሰፈሩትን መሠረታዊ ጉዳዮች በተግባር መዋል አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታመናል።

- ሀገሪቱን ከጥፋት ለማዳን፤ ከዘር ፖለቲካ በላይ ማሰብና መስራት የመጀመሪያ በር ከፋች ነው።

- ከዘር ፖለቲካ በላይ የሚያስቡ ዜጎችና ሃይሎች፤ በብሔራዊ / ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ዙሪያ ተነጋግሮ መስማማት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ጉዳይ ደግሞ ይዋል- ይደር የሚያሰኝ አይደለም ። እስካሁን ይህ ለምን አልተሞከርም ? ተሞክሮስ ከሆነ፤ ለምን ታዲያ ውጤት አላስገኘም ? የሚሉትን ዐውደ- ጥያቄዎች አንስቶ መወያይቱና ተገቢ መልሶች ማግኘቱ፤ ያለፈውን ስህተት ላለመድገም ይጠቅማል ።

- በኢትዮጵያዊ አጀንዳ ዙሪያ ለመነጋገርና ከአጥጋቢ ውሳኔም ላይ ለመድረስ ካስፈለገ፤ ከቂም-በቀልና ጥላቻ ራስን ነጻ ማደረግ የመጀምሪያው ርምጃ ነው። በዘረ- ድምር ላይ እያውጠነጠኑ የነጥብ አቸናፊነትን ለማግኘት መሞከር፤ ምናልባት የየግል ስሜቶችን ያረካ እንደሆነ እንጅ፤ ለአንድነትና ኅብረት መፈለጊያ የሚጠቅም አይሆንም ። ለሀገር-ለወገን የሚጠቅመው፤ በአትኩሮት ወደፊት እያሰቡ፤ ለመጭው ብሩኅ ተስፋ ተግቶ መሥራት እንደሚበጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተገነዘበው ቆይቷል ።

- ዛሬ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ቀዳማይ- በሄራዊ አጅንዳው ለሁሉም ዜጋ የምትሆን- የምትጠቅም አገር አድኖ መገንባትና የዕድገት ጎዳናን መቅየስ ነው። ለዚህ መሠርቱ ደግሞ፤ የሠላምና የዴሞክራሲ መስፈን የሚያጠያይቅ አልሆነም። የዘር ፖለቲካ ሥርዓት፤ ለሠላም፤ ለአንድነትና ለበሄራዊ ዕድገት ፤ ለዴሞክራሲና መረጋጋት ጠንቅ መሆኑ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ህያው ምስክር ሆናለች።

- አሮጌ አምባገነኖችን በአዲስ አምባገነኖች ላለመተካት ካስፈልገና፤ ብሎም፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት ከተሰበ፤ ሁሉንም ዜጋ ያከተተ የአንድነት ብሐራዊ ጉባዔ መዘጋጀት ወሳኝ ነው !

- ዞሮ ዞሮ ግን፡ " የሽ ፍልጥ፤ ማሰሪያው ልጥ " ነውና ፤ የኢትዮጵያ መጭው ሥርዓተ- መንግሥት መሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓ ት እንደሆነ አምኖ መታገል አማራጭ አይኖረውም። አምባገነን ሥርዓት በምንም ቅርፅና ይዘት ቢመጣ፤ እርሱን አስወግዶ፤ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካትም ካልሆነ በስተቀር ሌላ አማራጭ ሊኖር አይችልም ። በኢትዮጵያ የደሞክራሲ ሥርዓት ካልተመሰረተ ደግሞ ሠላምና ፀጥታ፤ ለማትና ዕደገት ይመጣል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። ይኽንን ሃቅ ተገንዝቦ ለደሞክራሲያዊ ሥረዓት መታገል ይሁሉም ዜጋ ሃላፊንትና ግዴታ ነው ።:

- ይህንን ሥርዓት ለማየት ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ጉጉት የጠብቃል ።

//////////////////////////// ---------------------- //////////////////////////